# የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት
# SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

# ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ
# THE DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA

፪ኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አርባምንጭ ታህሳስ ፳ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No 14
Arbaminch December, 2023


| **አዋጅ ቁጥር ፲፯/፪ሺ፲፮ ዓ.ም<br>የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዋጅ** | **Proclamation No. 17/2023<br>South Ethiopia Regional State Public Enterprises Proclamation** |
|---|---|
| የመንግስት የልማት ድርጅቶች ለክልሉ ኢኮኖሚያዊ ልማትና ዕድገት እንዲሁም ለክልሉ ሕዝቦች ሁለንተናዊ ዕድገት ገንቢ ሚና የሚኖራቸዉ በመሆኑ፤<br><br>በክልሉ በመንግስት ባለቤትነት የሚያዙና በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚሳተፉ የመንግስት ልማት ድርጅቶችና ተቋማትን ማቋቋም ስለታመነበት፤<br><br>በክልሉ መንግስት ባለቤትነትና ቁጥጥር ስር የሚቋቋሙ ድርጅቶችና ተቋማት በማምረት፣ በማከፋፈል፣ አገልግሎት በመስጠት፣ ግንባታና በመሣሰሉት ተግባራት ተሰልፈውና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ባለው መስክ አተኩረው በመሰማራት ለክልሉ ሁለንተናዊ ዕድገት ጉልህ አስተዋጽኦ | **WHEREAS,** public enterprises play a constructive role in the economic development and growth of the region as well as the overall development of the people of the region;<br><br>**WHEREAS,** it is believed to establish public enterprises and institutions that are owned by the state and participate in economic activities;<br><br>**WHEREAS,** it is necessary to establish and operationalize a system whereby public enterprises and institutions be established under the ownership and control of the regional government that are lined up and engage in economically viable activities to contribute |

| | |
|---|---|
| የሚያበረክቱበትን ስርዓት መዘርጋትና ገቢራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ | significantly to the overall development of the region through manufacturing, distribution, providing services, construction and similar activities; |
| በክልሉ የሚቋቋሙ የልማት ድርጅቶችና ተቋማት ለክልሉ ሁለንተናዊ ልማት ያላቸው ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ ካለመሆኑም በላይ ግዙፍ የመንግስት ፋይናንስ የሚፈስባቸው እንደመሆኑ መጠን በሚቋቋሙበት ዓላማዎች ልክ ከግሉ ዘርፍ ተቋማት ጋር በገበያ ተወዳዳሪዎች ሆነው በብቃት፣ በትርፋማነትና በውጤታማነት እንዲንቀሳቀሱ በማድረግና በማረጋገጥ መንግስትና ህዝብ ከዘርፉ የሚያገኙትን የላቀ ተጠቃሚነት እውን ማድረግ በማስፈለጉ፤ | **WHEREAS,** public enterprises and institutions having paramount significance, not only for their role in the overall development of the region, but also for the huge government finances poured into them, they need to realize the greater benefit that the government and the people get from them as envisaged in their establishment by making and ensuring that they operate efficiently, profitably, and effectively as competitors in the market with private sector institutions; |
| የልማት ድርጅቶች በክልሉ ሲቋቋሙ የተጠናከረና የተዋሀደ አመራርና ግልፅ የተልዕኮ አፈፃፀም አቅጣጫ የሚሠጣቸው ክልል አቀፍ የአመሰራረት፣ አደረጃጀት እና አሰራር ሥርዓትን በህግ መደንገግና የአሰራር ነጻነት የሚያገኙበትን ሥርዓት መዘርጋት፣ ማዘመንና ተጠያቂነት ያለበት ማድረግ እንዲሁም ከተቋቋመ በኃላ ሲፈርሱ ወይም ሲዋሀዱ ከግሉ ዘርፍና ከሌሎች ጋር በሽርክና አቀናጅቶ ለማሰራት ወይም ይዞታቸውን ሙሉ በሙሉ ወደ ግሉ ዘርፍ ለማስተላለፍ ወይም ለማዛወር የሚያስችል ህጋዊ አማራጭ ማበጀት አስፈላጊ በመሆኑ፤ | **WHEREAS,** it is necessary to institute a region-wide legal framework that will govern the establishment, organization, and systems of operation of public enterprises to enable them give strong and unified leadership and a clear direction for the execution of their mission, and institutional independence for their operation, modernization and accountability thereof, as well as operate in joint ownership with the private sector enterprises and others, or to transfer or redirect their holdings fully to the private sector, when a need arises to dissolve or merge; |
| የመንግስት ልማት ድርጅቶች አመሰራረት፣ አደረጃጀት፣ አመራርና ድጋፍ አሰጣጥን አሰራር ሥርዓት ለማሳለ□ □ተሟላ □ሕ□ ማ□ቀአ ማ□ጣትና መደንገግ ተ□ቢ ሆኖ በመ□ኘቱ፤ | **WHEREAS,** it is appropriate to issue and regulate a complete legal framework to facilitate the establishment, organization, management and providing support to public enterprises; |
| የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ ፶፬ ንዑስ አንቀፅ ፫(ሀ) ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል። | **NOW, THEREFORE,** the State Council of South Ethiopia issued this proclamation in accordance with the authority given under the provisions of Article 54 Sub-Article 3(a) of the Constitution of the Region. |

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩ አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፲፯/፪ሺ፲፮ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪ ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩ **"መንግስት"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ነው፤

፪ **"ድርጅት"** ማለት ሙሉ በሙሉ በክልሉ መንግስት ባለቤትነት ስር የዋለና በዚህ አዋጅ መሠረት በማምረት፣ በማከፋፈል፣ በግንባታ፣ አገልግሎት በመስጠት ወይም ማናቸውንም ሌላ ኢኮኖሚ ነክ ተግባር በመፈፀም ትርፍ ለማግኘት የተመሰረተ ወይም የሚመሰረት ተቋም ነው፤

፫ **"ተቆጣጣሪ ባለስልጣን"** ማለት የልማት ድርጅቶችን በተቀናጀ መንገድ ለመደገፍ፣ በተወዳዳሪነት መስራታቸውን ለማረጋገጥና ይልቁንም የክልሉ መንግስት በየትኛውም ድርጅት ላይ የሚኖሩትን የባለቤትነት መብቶች ለመጠበቅ ወይም ለማስከበር በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቋቋሙ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ድጋፍና ክትትል ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ነው፤

፬ **" የበላይ ኃላፊ"** ማለት የዚሁ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ኃላፊ ነው፤

፭ **"ጠቅላላ ንብረት"** ማለት የድርጅቱ ተንቀሣቃሽና ኢ-ተንቀሣቃሽ ሀብት ሲሆን የድርጅቱን ጥሬ ገንዘብ፣

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Public Enterprises Proclamation No. 17/2023".

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context dictates otherwise:

1) **"Government"** means the Regional Government of South Ethiopia;

2) **"Public Enterprise"** means an institution that is wholly owned by the state government established pursuant to this proclamation to earn profit by carrying out manufacturing, distribution, construction, providing services or any other economic activity;

3) **"Supervisory Authority"** means the support and monitoring authority of public enterprises established under this proclamation to support public enterprises in a coordinated way, to ensure that they work competitively and rather to protect or enforce the ownership rights of the state government in any enterprise;

4) **"Chief Head"** means the head of such supervisory authority;

5) **"Total Assets"** means the movable and immovable assets of the enterprise and includes cash, bank deposits, accounts receivables, intangible assets, prepaid expenses, and other accounts that are not

ተቀማጭ የባንክ ሂሣቦች፣ ተሰብሳቢ ሂሳቦች፣ ግዙፍነት የሌላቸዉ ንብረቶች፣ በቅድሚያ የተከፈሉ ወጪዎችና ወጪዎች ያልሆኑ ሌሎች ሂሣቦችን ያጠቃልላል፤

፮ **"የተጣራ ጠቅላላ ንብረት"** ማለት ከድርጅቱ ጠቅላላ ንብረት ላይ በተያዘው የሂሣብ ዓመት ውስጥ የተከፈሉት ዕዳዎች፣ በረዥም ጊዜ የሚከፈሉት ዕዳዎች፣ በቅድሚያ የተከፈለ ገቢና ሌሎች ዕዳዎች ተቀንሰው የሚቀረው ንብረት ነው፤

፯ **"መነሻ ካፒታል"** ማለት የትኛውም ድርጅት በተቋቋመበት ጊዜ በክልሉ መንግስት አማካኝነት የሚመደብለት የተጣራ ጠቅላላ ንብረት በተመደበበት ጊዜ ያለው ዋጋ ነው፤

፰ **"ካፒታል"** ማለት የትኛውም ድርጅት በተቋቋመበት ጊዜና ከዚያ በኋላ በክልሉ መንግስት አማካኝነት የሚመደብለት የተጣራ ጠቅላላ ንብረት በተመደበበት ጊዜ ያለው ዋጋ ነው፤

፱ **"የተጣራ ትርፍ"** ማለት ከገቢዎችና ከሌሎች ክፍያዎች ከተገኘው ገንዘብ ላይ ወጭዎችና በሂሣብ ዓመቱ ውስጥ ለስራ ማስኬጃም ሆነ ለደመወዝ ባግባቡ ወጭ የተደረጉ ሂሣቦች፣ የእርጅና ቅናሽ፣ ወለድና ልዩ ልዩ ታክሶች ተቀንሰው የሚቀረው ሂሣብ ነው፤

፲ **"ኦዲተር"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ /፴፪/ ስር በተመለከተው አኳኋን የየትኛውንም ድርጅት ሂሣብ እንዲመረምር የተሾመ የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፩ **"የመንግስት የትርፍ ድርሻ"** ማለት ከተጣራው ትርፍ ላይ ወደ ህጋዊ መጠባበቂያ ሂሣብና ሌሎች መጠባበቂያ ሂሣቦች ገቢ የሚደረገው ገንዘብ ተቀንሶ የቀረው ሂሣብ ነው፤

expenses;

6) **"Net total assets"** means the total assets of the enterprise minus the debts paid in the accounting year, long-term debts, unearned income, and other debts;

7) **"Initial capital"** means the value of the net total assets allocated to any public enterprise at the time of its establishment by the state government;

8) **"Capital"** means the prevailing value of the net total assets allocated to any public enterprise at the time of its establishment and anytime thereafter such net total assets are allocated by the state government;

9) **"Net profit"** means from the income and other payments earned during the year, the amount that remains after deducting reasonable expenses incurred during the accounting year for operating and salaries, depreciation, interest and miscellaneous taxes;

10) **"Auditor"** means a natural person or a body authorized by law to audit the accounts of any public enterprise in the manner referred to in Article 32 of this proclamation;

11) **"Government's share of profit"** means the balance left after deduction of the transfers to the legal reserve account and other reserve accounts from the net profit.

12) **"Board"** means the management board of any public enterprise established in accordance with the provisions of article /12/ of this proclamation.

| | |
|---|---|
| ፲፪ **“ቦርድ”** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ /፲፪/ ስር በተደነገገዉ መሠረት የሚቋቋም የየትኛውም ድርጅት የስራ አመራር ቦርድ ነው፤<br><br>፲፫ **“ሰዉ”** ማለት ማንኛዉም ተፈጥሯዊ ወይም ህጋዊ ሰዉነት ያለዉ ነዉ።<br><br>**፫ <u>የፆታ አገላለጽ</u>**<br><br>በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይመለከታል።<br><br>**፬ <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**<br><br>የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ይህ አዋጅ ከመውጡቱ በፊት የተቋቋሙ የልማት ድርጅቶች እና አዋጁ ከወጣ በኂላ በሚቋቋሙ የልማት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።<br><br>**፭ <u>ስለ ሌሎች ህጐች ተፈፃሚነት</u>**<br><br>በዚህ አዋጅ ውስጥ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው የሀገሪቱ የፍትሐብሔርና የንግድ ህጐች ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በተቋቋሙት ወይም በሚቋቋሙት ድርጅቶች ላይም በተመሣሣይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ። | 13) **“Person”** means any natural or juridical person.<br><br>**3. <u>Gender Reference</u>**<br><br>In this proclamation, any expression of the male gender refers to the female gender as well.<br><br>**4. <u>Scope of Application</u>**<br><br>The provisions of this proclamation shall apply to public enterprises established before the promulgation of this decree and to public enterprises established after the promulgation of this decree.<br><br>**5. <u>Applicability of Other Laws</u>**<br><br>Unless otherwise determined in this proclamation, the relevant provisions of the civil and commercial laws of the country shall be equally applicable to the enterprises established or to be established in accordance with this proclamation. |
| **<u>ክፍል ሁለት</u>**<br><br>**<u>ስለ ድርጅቶች አመሰራረት፣ ህጋዊ ሰውነትና ችሎታ</u>**<br><br>**፮ <u>በድርጅት ምስረታ ወቅት መሟላት ስላለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች</u>**<br><br>፩ ማናቸውም ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት ከመቋቋሙ በፊት ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡-<br><br>ሀ/ በካፒታልነት የተከፈለ ጥሬ ገንዘብ ያለ እንደሆነ ይኸው በሚቋቋመው ድርጅት ስም በተከፈተ | **<u>PART TWO</u>**<br><br>**<u>ESTABLISHMENT, LEGAL PERSONALITY, AND CAPACITY OF PUBLIC ENTERPRISES</u>**<br><br>**6. <u>Requirements to be met before Establishment of a Public Enterprise</u>**<br><br>1) Before any enterprise is established under this proclamation, the supervisory authority shall ensure that the following conditions are met:<br><br>a) Any cash paid as part of the capital is deposited in a bank in the name and to the account of the |

የባንክ ሂሣብ ተቀማጭ የተደረገ መሆኑን፤

ለ/ በዓይነት የተደረገ ክፍያ ያለ እንደሆነ ይኸው ንብረት በባለሙያዎች አማካኝነት በትክክል የተገመተ መሆኑን፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /፩/ ፊደል ተራ ቁጥር /ለ/ ስር የተደነገገው ቢኖርም በዓይነት የተደረገው ክፍያ አስቀድሞ በኦዲተር የተረጋገጠ ሂሣብ ያለው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ግምቱ በዚሁ ሂሣብ መዝገብ መሠረት ሊያዝ ይችላል፤

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /፩/ ፊደል ተራ ቁጥር /ለ/ ስር የተመለከቱት ባለሙያዎች የንብረቱን ዝርዝር የያዘ መግለጫ፣ ለእያንዳንዱ የንብረት ክፍል የተሰጠውን ዋጋና ያገማመቱን ዘዴ የያዘ ዘገባ ያዘጋጃሉ፡፡

፬ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በነባሩ ክልል ህግ የተቋቋመ ድርጅት ሁኔታ በተመለከተ የዚሁ ድርጅት የክልላችን ስራ አመራርና ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ እያንዳንዳቸው ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ዘገባ አንዳንድ ኮፒ ያገኛሉ፤

፭ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፬/ መሰረት ማናቸውም ድርጅት በዚህ አዋጅ ከመቋቋሙ በፊት ከነባሩ ክልል ለክልላችን በድርሻ ልክ ለድርጅቱ የሚያዝ ሀብት ካለና ይኸው በኦዲተሮች የተረጋገጠ ከሆነ ለሚቋቋመው ድርጅት በካፒታልነት ይታሰባል፤

፮ ማናቸውም ድርጅት ከመቋቋሙ በፊት ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ለድርጅቱ ምስረታ አስቀድሞ ያደረገው ወጭ ካለና ይኸው በኦዲተሮች የተረጋገጠ ከሆነ ለሚቋቋመው

enterprise;

b) Any payment made in kind as part of the capital is valued properly by experts;

2) Notwithstanding sub-article 1 (b) of this Article, if the payment made in kind has audited accounts, the book value of such payment in kind may be taken into account.

3) The experts appointed under sub-article 1 (b) of this Article shall prepare a report containing a detailed description of the property, the value given to each item, and the method of valuation. The supervisory authority and the enterprise shall get one copy each of such report.

4) For a public enterprise that was established before the issuance of this proclamation in the former region by the then regional law, the management of the enterprise representing our region and the supervisory authority shall each receive a copy of the above-mentioned report;

5) According to sub-article 4 of this article, for any public enterprise from the former region that existed before the issuance of this proclamation, if there is a share of wealth for the enterprise in our region and if that is confirmed by the auditors, it shall be considered as capital for the enterprise to be established;

6) If there are any expenses incurred by the supervisory authority for but prior to the establishment of any enterprise and confirmed by auditors, such expenses shall be considered as part of capital of the enterprise to be established;

7) The sums deposited under sub-article 1 (a) of this Article shall not be withdrawn from the bank until

ድርጅት በካፒታልነት ይታሰባል፤

፯ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /፩/ ፊደል ተራ ቁጥር /ሀ/ ስር የተመለከተው ተቀማጭ የባንክ ሂሣብ የድርጅቱ ማቋቋሚያ ደንብ በክልሉ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እስኪወጣና ተግባራዊ እስኪደረግ ድረስ ወጭ ሊደረግ አይችልም።

## ፯ ስለ ማቋቋሚያ ደንብ

፩ ማናቸውም ድርጅት የሚቋቋመው በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይሆናል፤

፪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፩/ መሠረት በሚወጣው የድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ውስጥ የሚከተሉት ዝርዝር ጉዳዩች መካተት ይኖርባቸዋል፡-

ሀ/ የድርጅቱ መጠሪያ ስም፤
ለ/ ድርጅቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚተዳደር ስለመሆኑ የሚያመለክት መግለጫ፤
ሐ/ ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች፤
መ/ የድርጅቱ የተፈቀደ ካፒታል፤
ሠ/ ከድርጅቱ መነሻ ካፒታል ውስጥ በጥሬ ገንዘብም ሆነ በዓይነት የተከፈለው ድርሻ መጠን፤
ረ/ ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ የሚደረግ ስላለመሆኑ የሚያመለክት መግለጫ፤
ሰ/ የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት፤
ሸ/ ድርጅቱ ቅርንጫፎችን ለመክፈት ስለሚኖረው ስልጣን የሚያመለክት መግለጫ፤
ቀ/ ድርጅቱ በስራ ላይ የሚቆይበት መዋዕለ-ዘመን።

## ፰ ህጋዊ ሰውነትና ችሎታ

፩ የትኛውም ድርጅት ህጋዊ ሰውነት ያለው ሆኖ ይቋቋማል፤ በዚህም አቋሙ ምክንያት በነፃነት የሚሰራባቸው መብቶችና ግዴታዎች ይኖሩታል፤

the establishment regulation of the enterprise are published and implemented in the Negarit Gazette of the State Government.

## 7. Establishment Regulation

1) Any public enterprise shall be established by a regulation issued pursuant to this Proclamation;
2) The following detailed issues shall be included in the establishment regulation issued in accordance with sub-article /1/ of this article:
   a) the name of the enterprise;
   b) a statement that the enterprise shall be governed by this Proclamation;
   c) the purpose for which the enterprise is established;
   d) the authorized capital of the enterprise;
   e) the amount of capital paid up in cash and in kind from the initial capital of the enterprise;
   f) a statement that the enterprise shall not be liable for debts exceeding its total assets;
   g) the head office of the enterprise;
   h) a statement that the enterprise shall have the authority to open branches;
   i) the period during which the enterprise remains in business.

## 8. Legal Personality and Capacity

1) Any public enterprise shall be established as having an autonomous legal personality, and due to this stand shall have the rights and obligations to act freely;
2) Any public enterprise shall have the capacity necessary to achieve the objectives for which it was established and carry out activities related to these objectives;

፪ ማናቸውም ድርጅት የተቋቋመባቸውን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስና ከነዚሁ ዓላማዎች ጋር ተዛማጅ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስፈልገው ችሎታ ሁሉ ይኖረዋል፤

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /፪/ ስር የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ድርጅት፡-

ሀ/ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤

ለ/ የሚንቀሣቀስና የማይንቀሣቀስ ንብረት የማፍራት፣ ባለይዞታ ወይም ባለቤት የመሆን፣ ለሶስተኛ ወገኖች የማስተላለፍ ወይም በዕዳ የማስያዝ፤

ሐ/ ውሎችን የመዋዋልና ገንዘብ የመበደር፤

መ/ ንግድ ነክና ሌሎች ተመሣሣይ ሰነዶችን የማውጣትና የመቀበል፤

ሠ/ በልዩ ልዩ መስኮች መዋዕለ-ንዋዩን ኢንቨስት የማድረግ፤ ችሎታ አለዉ፡፡

3) Without prejudice to the general assertion stated under sub-article /2/ of this article, any public enterprise shall have the capacity to:

a) sue and be sued in its own name;

b) acquire, possess or own, transfer to third parties or mortgage any movable and immovable property;

c) negotiating contracts and borrow money;

d) issue and receive commercial and other similar documents;

e) invest in various fields.

**፱ <u>በዕዳ ስላለመጠየቅ</u>**

ማናቸውም ድርጅት ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም፡፡

**9. <u>Liability</u>**

No public enterprise shall be liable beyond its total assets.

**፲ <u>ስለ ዋና አድራሻና ቅርንጫፎች</u>**

የማናቸውም ድርጅት አድራሻ ዋና መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ስፍራ ሲሆን አስፈላጊ በሆኑ አካባቢዎች ቅርንጫፍ ወይም ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

**10. <u>Address of the Head Office and Branches</u>**

The address of any public enterprise shall be the place where its head office is situated, and may have branches or coordination offices elsewhere in the country as may be necessary.

## ክፍል ሶስት
## ስለ ድርጅቶች አወቃቀርና ስራ አመራር

**፲፩ <u>አወቃቀር</u>**

እያንዳንዱ ድርጅት ከዚህ በታች የተመለከቱት አበይት አካላት ይኖሩታል፡-

## PART THREE
## ORGANIZATION AND MANAGEMENT OF PUBLIC ENTERPRISES

**11. <u>Organization</u>**

Each public enterprise shall have the following main components:

፩ የሥራ አመራር ቦርድ፤

፪ ዋና ሥራ አስኪያጅና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ሥራ አሥኪያጅ፤ እና

፫ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች የበታች ስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፡፡

**፲፪ <u>ስለ ስራ አመራር ቦርድ አመሰራረት፣ የአባላት ተዋጽኦና የአገልግሎት ዘመን</u>**

፩ እያንዳንዱ ድርጅት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የሚኖረው ተጠሪነት እንደተጠበቀ ሆኖ ስራዎቹን በበላይነት የሚያስተባብርና በዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ እየመከረ ውሣኔዎችን የሚያሳልፍ የራሱ ስራ አመራር ቦርድ ከዚህ በኃላ “ቦርዱ” እየተባለ የሚጠራ አካል ይኖረዋል፤

፪ የቦርዱ አባላት ቁጥር ቢያንስ ሰባት ሆኖ ከፍተኛው ደግሞ ከአስራሁለት ያልበለጠ ይሆናል፤

፫ የቦርዱ አባላት ሰብሳቢዉን ጨምሮ አግባብነት ካላቸዉ አካላት ተዉጣጥተዉ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሰየማሉ፤

፬ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የበላይ ኃላፊዉ ከድርጅቱ ሠራተኞች አንድ ተወካይ የዚሁ ቦርድ አባል አድርጐ ሊሰይም ይችላል፤

፭ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፫/ ስር የሰፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቦርድ አባላቱ አሰያየምና አመራረጥ በሙያ፣ በስራ ልምድና በግል ብቃት ላይ ተመስርቶ የሚፈፀም ይሆናል፤

፮ ማንኛውም የቦርድ አባል ተወዳዳሪ ያልሆነ የሌላ ድርጅት ቦርድ አባል ሆኖ እንዲያገለግል ሊሰየምና ተጨማሪ ተልዕኮ ሊሰጠው ይችላል፤

፯ የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን ከሶስት አመት የማያንስና ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ይሆናል፡፡ ሆኖም አስፈላጊነቱ ሲታመንበት ማንኛውም የቦርድ አባል የአገልግሎት ጊዜው ሲያበቃ ለሁለተኛ ጊዜ ብቻ

1) Management Board;
2) General Manager and Deputy General Manager as necessary; and
3) Other subordinates and staff necessary for the work.

**12. <u>Establishment of the Board, Composition of the Members and Term of Service</u>**

1) Without prejudice to maintaining accountability to the supervisory authority established pursuant to this proclamation, each public enterprise shall have its own management board, hereinafter referred to as the "Board", which will coordinate its operations and make decisions on major policy issues.
2) The number of members of the board shall be at least seven and the maximum shall not exceed twelve;
3) The members of the board, including the chairman, are selected from the relevant bodies and appointed by the head of the state;
4) When deems it appropriate, the superior head of the supervisory authority shall appoint a representative from the enterprise's employees as a member of the board;
5) Without prejudice to the general provision stipulated under sub-article /3/ of this Article, the appointment and selection of the board members shall be done in regard to their profession, work experience and personal competence;
6) Any board member may be appointed and assigned additional duties to serve as a board member of another non-competing enterprise;
7) The term of office of board members shall be not less than three years and not more than five years. However, when deemed necessary, any board

ሊሰየም ወይም ሊመረጥ ይችላል፤

፰ የድርጅቱ የስራ እንቅስቃሴ ቀጣይነት ይኖረው ዘንድ የቦርድ አባላቱ የአገልግሎት ዘመን በአንድና በተመሣሣይ ጊዜ አያበቃም፤

፱ ማንኛውም የቦርድ አባል አባልነቱን በገዛ ፈቃዱ የተወ እንደሆነ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ አባልነቱን የተወው ይኸው አባል በተተኪ ሌላ አባል እንዲተካ ጉዳዮን ለርዕሰ መስተዳደሩ ያቀርባል፤

፲ ተገቢነት ያለው ስላለመሆኑ በቂ ምክንያት ሲኖረው ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የትኛውንም የቦርድ አባል በማናቸውም ጊዜ ከአባልነቱ እንዲነሳ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ በሰራተኛ ማህበር ተወካይነቱ የተሰየመውን ማንኛውንም የቦርድ አባል በሚመለከት ተፈፃሚ ሲደረግ ማህበሩ ስለጉዳዩ አስቀድሞ እንዲያውቅ መደረግ ይኖርበታል፡፡

## ፲፫ የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ /፵፯/ መሠረት ለተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ መቅረብ ከሚገባቸው በስተቀር በሌሎች የድርጅቱ ፖሊሲ ነክ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ውሣኔዎችን ያሳልፋል፤

፪ የድርጅቱን ዋና ስራ አስኪያጅ ይመድባል፣ ደመወዝና አበሉን ይወስናል፣ ከስራ ያሰናብታል፤

፫ ለድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑ የስራ ኃላፊዎችን ቅጥር፣ ምደባና ስንብት መርምሮ ያፀድቃል፣ ደመወዝና ጥቅማጥቅሞቻቸውን ይወስናል፤

member may be nominated or elected for a second term only upon the expiration of his term of office;

8) In order to ensure the continuity of the enterprise's activities, the term of service of the board members shall not end at one and the same time.

9) Where any member of the board resigns from membership by own will, the supervisory authority will present the matter to the chief executive of the state for the member to be replaced by another member.

10) Whereas there is sufficient reason for its inappropriateness, the supervisory authority may submit a request to the chief executive of the state to remove any member of the board at any time. However, when this provision is implemented in relation to any board member designated by the employees' association, the association shall be informed in advance about the matter.

## 13. Powers and Duties of the Board

The Board shall have the following powers and duties pursuant to this Proclamation:-

1) Deliberates on and passes decisions on other policy related issues of the enterprise, except for those issues that should be submitted to the supervisory authority as stipulated in article /47/ of this Proclamation;

2) Recruits, appoints, assigns and dismisses the General Manager of the enterprise and determines the salary and allowances;

3) Examines and approves the hiring, assignment and dismissal of officials who are accountable to the general manager of the enterprise, and determines their salaries and benefits;

4) Examines and approves drafts of the enterprise's

፬ የድርጅቱን የውስጥ ደንብ፣ የስራ ዕቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቆች መርምሮ ያፀድቃል፤

፭ የድርጅቱን የረዥም ጊዜ ብድሮች ያፀድቃል፤

፮ በድርጅቱ ህልውና ላይ ወሳኝነት የሌላቸውን ቋሚ ንብረቶች ሽያጭ ያፀድቃል፤

፯ የድርጅቱ ሂሣቦችና ንብረቶች ባግባቡ መያዛቸውንና መጠበቃቸውን ያረጋግጣል፤

፰ የድርጅቱ ካፒታል ይጨምር ወይም ይቀንስ ዘንድ ለተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ሐሣብ ያቀርባል።

**፲፬ <u>ስለ ቦርዱ የስብሰባ ጊዜና የውሣኔ አሰጣጥ ስነ-ሥርዓት</u>**

፩ ቦርዱ መደበኛ ስብሰባውን ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ያካሄዳል፤ሆኖም አስቸኳይ ጉዳዮች ሲያጋጥሙት አስቸኳይ ስብሰባዎችን ከዚህ ባነሰ ጊዜ ከማካሄድ አይታገድም፤

፪ የቦርድ አባላት ስብሰባው ከመካሄዱ በፊት የመወያያ አጀንዳው በጹሑፍ ተዘጋጅቶ እንዲደርሳቸው ያስፈልጋል፤

፫ ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ የተገኙ እንደሆነ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፤

፬ ማናቸውም ጉዳይ ለቦርዱ ቀርቦ ከተመከረበት በኃላ በስብሰባው ላይ በተገኙት አባላት የአብላጫ ድምፅ የተደገፈ እንደሆነ የቦርዱ ውሣኔ ሆኖ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል ለኩል የተከፈለ እንደሆነ የሰብሳቢውን ድጋፍ ያገኘው ሀሣብ የቦርዱ ውሣኔ ይሆናል፤

፭ ቦርዱ ከድርጅቱ ሰራተኞች መካከል ፀሀፊውን መርጦ ሊመድብ ይችላል፤

፮ ፀሀፊው ቦርዱ የሚያካሂደውን የእያንዳንዱን ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ በሚገባ ይይዛል፣ በስብሰባው ላይ የተገኙት አባላትም በቃለ-ጉባኤው ላይ ይፈርሙበታል፤

internal regulations, work plan and budget for implementation of the same;

5) Approves long-term loans of the enterprise;

6) Approves the sale of fixed assets that are not critical to the existence of the enterprise;

7) Ensures that the enterprise's accounts and assets are properly maintained and protected;

8) Proposes to the supervisory authority to increase or decrease the enterprise's capital.

**14. <u>Timing of Board Meeting and Decision Making Procedure</u>**

1) The board shall hold its regular meeting at least once every three months; however, when faced with urgent matters, it shall not be prohibited to hold emergency meetings less frequently.
2) It is required that the board members receive the agenda in writing before the meeting.
3) If more than half of the board members are present at the meeting, it will be a quorum;
4) After any issue has been presented to the board and discussed up on, it will be passed on as a decision of the board if supported by the majority of the members present at the meeting. However, if the vote is equally divided, the decision of the board shall be the opinion supported by the chairman;
5) The board may choose and appoint the secretary from among the enterprise's employees;
6) The secretary shall keep the minutes of each meeting held by the board, and the members present at the meeting shall sign on the minutes;
7) The general manager of a public enterprise may attend and participate in the board meetings; however, shall not have the right to vote on any of

፯ የድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ በቦርዱ ስብሰባዎች ላይ በአካል ሊገኝና ሊሳተፍ ይችላል፤ ሆኖም ቦርዱ በሚያሳልፋቸው ማናቸውም ውሣኔዎች ድምፅ የመስጠት መብት አይኖረውም፤

፰ በዚህ አንቀጽ ከዚህ በላይ የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን ውስጣዊ የስብሰባ ጊዜና የውሣኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት ደንብ ሊያወጣና በስራ ላይ ሊያውል ይችላል።

## ፲፭ ስለ ቦርድ አባላት ተጠያቂነት

፩ የቦርድ አባላት በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጧቸውን ተግባራት በከፍተኛ ትጋትና በብርቱ ጥንቃቄ መፈፀም አለባቸው፤

፪ አባላቱ ተግባራቸውን በአግባቡ ካለመፈፀማቸው የተነሣ በድርጅቱ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በአንድነትና በነጣላ ተጠያቂዎች ይሆናሉ።

## ፲፮ ስለ ዋና ስራ አስኪያጁ ስልጣንና ተግባር

፩ የድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የድርጅቱን ስራዎች በሀላፊነት ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ /፲፫/ ንዑስ አንቀፅ /፫/ ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ የበታች ስራ ሀላፊዎችን ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ተግባራቸውን ይወስናል፤

ሐ/ በድርጅቱ የውስጥ ደንብና አግባብ ባለው ህግ መሠረት ሌሎች የድርጅቱን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ያዛዉራል፣ ያሰናብታል፣ ደመወዝና አበሎቻቸውን ይወስናል፤

መ/ በድርጅቱ ስም የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፣ ያንቀሣቅሳል፤

the resolutions the board passes on;

8) Without prejudice to the provisions stipulated herein above in this Article, the board may establish and implement its own internal guidelines regarding the timing of meetings and decision-making procedures.

## 15. Accountability of Board Members

1) Members of the board shall perform their duties with utmost diligence and due care;
2) The members shall be liable jointly and severally for the damage caused to a public enterprise due to their failure to perform their duties properly.

## 16. Powers and Duties of the General Manager

1) The general manager of the public enterprise shall have the following powers and duties pursuant to this proclamation:-
   a) Responsibly organizes, directs, coordinates and supervises the activities of the enterprise;
   b) Without prejudice to the provisions stipulated in Article /13/ sub-article/3/ of this proclamation, hires, assigns and determines the duties of subordinate accountable to him;
   c) Hires, assigns, transfers, dismisses, and determines the salaries and allowances of other employees in accordance with the public enterprise's internal regulations and other relevant laws;
   d) Opens and runs a bank account in the name of the enterprise;
   e) Enters into short-term loan contracts for the purpose of providing the working capital of the enterprise, borrows money on a long-term basis upon approval of the board, and for those purposes upon approval by the board presents as collateral

ሠ/ ለድርጅቱ ስራ ማስኬጃ የሚውሉ የአጭር ጊዜ ብድር ውሎችን ይዋዋላል፣ ቦርዱን በማስፈቀድ የረዥም ጊዜ ብድር ይወስዳል፣ ለእነዚሁ ዓላማዎች ቦርዱን እያስፈቀደ የድርጅቱን የሚንቀሣቀስ ወይም የማይንቀሣቀስ ንብረት በዕዳ መያዣነት ሊሰጥ ይችላል፤

ረ/ የድርጅቱን የስራ ፕሮግራምና በጀት እንዲሁም የውስጥ ደንብ ረቂቅ አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

ሰ/ ቦርዱን በቅድሚያ በማስፈቀድ በድርጅቱ ህልውና ላይ ወሳኝ ተፅዕኖ የሌላቸውን ቋሚ ንብረቶች ይሸጣል፤

ሸ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ድርጅቱን ይወክላል፤

ቀ/ የቦርዱን ውሣኔዎች ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፤

በ/ የስራ እንቅስቃሴውን በሚመለከት ሪፖርቶችን በየወቅቱ እያዘጋጀ ለቦርዱ ያቀርባል፤

ተ/ ለስራው አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው መጠን ከስልጣንና ተግባራቱ ከፊሉን ለድርጅቱ የበታች ስራ ሀላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

ቸ/ በድርጅቱ የስራ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚመክርና በርምጃውም ሆነ በዕቅዶቹና በውሣኔዎቹ ላይ የሚወያይ የስራ አመራር ኮሚቴ ሊያቋቁምና ስብሰባዎቹን በበላይነት ሊመራ ይችላል፤

ነ/ በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

፪ የድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል።

**፲፯ ስለ ዋና ስራ አስኪያጁ ሀላፊነትና ተጠያቂነት**

የድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ በዚህ አዋጅ መሠረት ተግባሩን

the movable or immovable property of the enterprise;

f) Prepares the enterprise's work program and budget as well as internal regulation drafts and submits it to the board, and when approved, implements it;

g) Sell fixed assets that do not have a significant impact on the enterprise's existence with the prior approval of the board;

h) Represents the enterprise in dealings with third parties;

i) Executes and makes executed the decisions of the board;

j) Prepares and submits reports to the board periodically with regard to activities of the enterprise;

k) Delegates part of the powers and duties to the subordinates and employees of the enterprise to the extent that he finds it necessary for the work;

l) Establishes a management committee that deliberates on the enterprise's activities and discusses its actions, plans and decisions and presides over its meetings;

m) Performs other related duties as assigned by the board.

2) The general manager of the public enterprise will be accountable to the board.

**17. Responsibility and Liability of the General Manager**

The general manager of the enterprise shall be liable for the damage he causes to the enterprise intentionally or negligently whenever he performs his duties pursuant to this proclamation.

**18. Agency**

Any public enterprise performing its tasks, obtaining its

| | |
|---|---|
| በሚፈፅምበት ጊዜ ሁሉ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት በድርጅቱ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፡፡<br><br>**፲፰ <u>በውክልና ስለመስራት</u>**<br><br>የትኛውም ድርጅት ስራዎቹን የሚያከናውነው፣ መብቶቹን የሚያገኘውና ግዴታዎቹን የሚፈፅመው በዚህ አዋጅ ከዚህ በላይ በሰፈሩት ድንጋጌዎች መሠረት ስልጣን በተሰጣቸው በዋና ስራ አስኪያጁና በሌሎች የስራ ኃላፊዎች አማካኝነት በመወከል ይሆናል፡፡ | rights, and executing its obligations in accordance with the above provisions of this decree will be through representation by the general manager and other authorized officials. |
| **<u>ክፍል አራት</u>**<br>**<u>ስለ ድርጅቱ ካፒታል</u>**<br><br>**፲፱ <u>ድርጅቱን ለማቋቋም ስለሚያስፈልገው ካፒታል</u>**<br>፩ ማናቸውም ድርጅት የራሱ ካፒታል ይኖረዋል፤<br>፪ ማናቸውም ድርጅት ለመቋቋም የሚያስፈልገው መነሻ ካፒታል በተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ አማካኝነት ቀርቦ በክልሉ መንግስት እንዲመደብ ይደረጋል፤<br>፫ ካፒታሉ በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ ሊሆን ይችላል፡፡ በአይነት የተከፈለ ከሆነ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ /፮/ ንዑስ አንቀፅ /፩/ ፊደል ተራ ቁጥር /ለ/ መሠረት የተገመተ ወይም በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /፪/ መሠረት በባለሙያዎች አማካኝነት በትክክል የተጣራ ስለመሆኑ ያረጋግጣል፡፡<br><br>**፳ <u>ስለተከፈለና ስለተፈቀደ ካፒታል</u>**<br><br>፩ የትኛውም ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት ሲቋቋም የሚኖረው የተከፈለ ካፒታል መጠን ከተፈቀደለት መነሻ ካፒታል 25 በመቶ ያነሰ ሊሆን አይችልም፤<br>፪ አንድ ድርጅት መነሻ እንዲሆነው የተፈቀደለት ጠቅላላ ካፒታል ድርጅቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በ፭ ዓመት ውስጥ በሙሉ ተከፍሎ ማለቅ ይኖርበታል፤ | **<u>PART FOUR</u>**<br>**<u>CAPITAL OF PUBLIC ENTERPRISES</u>**<br><br>**19. <u>Capital required to Establish a Public Enterprise</u>**<br>1) Any enterprise shall have its own capital;<br>2) The initial capital needed to establish any public enterprise shall be presented through the supervisory authority and will be allocated by the state government;<br>3) The capital may be in kind or cash. If it is paid in kind, the supervisory authority shall verify whether it is valued in accordance with Sub-Article /1b/ of Article /6/ of this decree or whether it is properly verified by experts in accordance with Sub-Article /2/ of the same article.<br><br>**20. <u>Paid-up and Authorized Capital</u>**<br><br>1) The amount of paid-up capital of any public enterprise established under this decree shall not be less than 25% of the authorized initial capital;<br>2) The total capital authorized to start a public enterprise shall be paid in full within 5 years from the time the enterprise was established;<br>3) If the authorized capital is not paid in full within the time limit specified under sub-article /2/ of this |

፫ የተፈቀደለት ካፒታል በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፪/ ስር በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በሙሉ ተከፍሎ ካልተጠናቀቀ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የሶስተኛ ወገኖች መብት ሣይነካ የድርጅቱ ካፒታል ወደተከፈለው የካፒታል መጠን ዝቅ እንዲል ያደርጋል፡፡

**፳፩ <u>የተፈቀደን ካፒታል ስለመጨመር</u>**

ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ከድርጅቱ ገቢ ውስጥ ተቀናሽ እንዲሆን በማድረግ ወይም ከክልሉ መንግስት በኩል መዋዕለ-ንዋይ በማስመደብ የድርጅቱ ካፒታል እንዲጨምር ሊያደርግ ይችላል፡፡

**፳፪ <u>ካፒታል ስለመቀነስ</u>**

የየትኛውም ድርጅት ካፒታል የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የሶስተኛ ወገኖች መብት ሣይነካ ተቀናሽ እንዲሆን ሊደረግ ይችላል፡-

፩ የድርጅቱ ካፒታል እንዲቀነስ ኦዲተሮች ሲያሳስቡ፤

፪ ቦርዱ በሚያቀርበው ሀሣብ መሠረት ካፒታሉ እንዲቀነስ በተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ሲወሰን፤

፫ የድርጅቱ የተፈቀደ ካፒታል በዚህ አዋጅ አንቀጽ /፳/ ንዑስ አንቀፅ /፪/ መሠረት በሙሉ ተከፍሎ ያላለቀ ሲሆን፡፡

article, the supervisory authority shall, without prejudice to the rights of third parties, adjust the enterprise's capital to the amount of paid-in capital without affecting.

**21. <u>Increasing the Authorized Capital</u>**

The supervisory authority might make the enterprise's capital to increase by making a deduction from the enterprise's income or through making resources be allocated by the state government.

**22. <u>Decrease of Capital</u>**

The capital of any public enterprise may, without prejudice to the rights of third parties, decrease in the following cases:

1) When the auditors recommend that the enterprise's capital be decreased;

2) When it is decided by the supervisory authority to decrease the capital pursuant to the proposal of the board;

3) When the authorized capital of the enterprise has not been paid in full according to sub-article /2/ of Article /20/ of this decree.

## <u>ክፍል አምስት</u>
## <u>ስለ ድርጅቱ ስምና የንግድ ምልክት</u>

**፳፫ <u>የድርጅቱ መጠሪያ ስም</u>**

፩ የአንድ ድርጅት መጠሪያ ስም ስራውን ሲያከናውን የሚታወቅበት ስም ሲሆን የድርጅቱን ስራ በግልፅ የሚያመለክት ይሆናል፤

፪ የየትኛውም ድርጅት ስም የመንግስት ፖሊሲን እንዲሁም መልካም ስነ-ምግባርን የሚቃረን ወይም

## <u>PART FIVE</u>
## <u>NAME AND TRADEMARK OF A PUBLIC ENTERPRISE</u>

**23. <u>Name of a Public Enterprise</u>**

1) The name of a public enterprise shall be the name by which it is known when performing its activities and shall clearly indicate such activities;

2) The name of any public enterprise shall not be found

የሶስተኛ ወገኖችን መብት የሚፃረር ሆኖ መገኘት አይኖርበትም፤

፫ ማናቸውም ድርጅት መጠሪያ ስሙን በቅጥር ግቢው ውስጥ በግልፅ በሚታይ ስፍራ መስቀልና ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ ይኖርበታል፡፡

**፳፬ <u>በስም አጠቃቀም ረገድ ስለሚጣሉ ገደቦች</u>**

፩ የአንድ ድርጅት ስም አመራረጥ በዚህ አዋጅ አንቀፅ /፳፫/ ንዑስ አንቀፅ /፪/ ስር በተመለከተው መሠረት መሆኑን ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ያረጋግጣል፤

፪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ /፳፫/ ንዑስ አንቀፅ /፪/ ስር የተመለከተውን ገደብ ተላልፎ የተገኘ ማናቸውም ድርጅት ላደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍልና ክርክር ባስነሳው መጠሪያ ስም እንዳይጠቀም በፍርድ ቤት ሊወሰን ይችላል፡፡

**፳፭ <u>የንግድ ምልክት</u>**

የንግድ ምልክት አንድ ድርጅት ለሚያመርተው ዕቃ ወይም ለሚሰጠው አገልግሎት መለያ በማድረግ የሚጠቀምበት ስያሜ፣ ዓርማ ወይም ሌላ ማናቸውም አይነት መለያ ምልክት ነው፡፡

**፳፮ <u>በንግድ ምልክት አጠቃቀም ረገድ ስለሚጣሉ ገደቦች</u>**

፩ ማናቸውም ድርጅት የትኛውንም ዓይነት የንግድ ምልክት ሊመርጥ ይችላል፤

፪ ማናቸውም የንግድ ምልክት የመንግስትን ፖሊሲ እንዲሁም መልካም ስነ-ምግባርን የሚቃረንና የሶስተኛ ወገኖችን መብት የሚነካ ሆኖ መገኘት አይኖርበትም፤

፫ የማናቸውም ድርጅት የንግድ ምልክት በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት አግባብ ባለው የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤት ይመዘገባል፣ በሰፊው በሚሰራጭ ክልል አቀፍ ጋዜጣም ታትሞ ይወጣል፤

፬ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፪/ ስር የተመለከተውን ተላልፎ የተገኘ ማናቸውም ድርጅት ላደረሰው ጉዳት

to be against government policy and good ethics or against the rights of third parties;

3) Any public enterprise shall display its name in a clearly visible place in the premises and make it accessible to the public.

**24. <u>Restrictions on the Use of Names</u>**

1) The supervisory authority confirms that the selection of a public enterprise's name is based on the provisions of Sub-Article /2/ of Article /23/ of this Proclamation;
2) Any enterprise found to have violated the restrictions mentioned under Sub-Article /2/ of Article /23/ of this Decree may be ordered by the court to pay compensation for the damage and not to use the name that has caused a dispute.

**25. <u>Trademark</u>**

A trademark is a name, emblem, or any other designation used by a public enterprise to identify the goods it produces or the services it provides.

**26. <u>Restrictions on the Use of Trademarks</u>**

1) Any public enterprise may choose any trademark;
2) Any trademark should not be found to be against government policy and good morals and affect the rights of third parties;
3) Before any enterprise's trademark goes into effect, it shall be registered with the relevant regional government office and published in a widely distributed regional newspaper;
4) It may be decided by the court that any public enterprise found to be in violation of this article shall pay compensation for the damage caused and

| | |
|---|---|
| ካሣ እንዲከፍልና ክርክር ባስነሳው የንግድ ምልክት እንዳይገለገል በፍርድ ቤት ሊወሰን ይችላል፡፡ | not be used by the disputed trademark. |

**ክፍል ስድስት**
**ስለ ድርጅቶች ሂሣብና የቁጥጥር ስርዓት**

**ንዑስ ክፍል አንድ**
**ስለ ድርጅቶች ሂሣብ**

**፳፯ ስለ ሂሣብ አያያዝ መርሆዎች**

የትኛውም ድርጅት በንግድ አሰራር ተቀባይነት ያላቸውን የሂሣብ አያያዝና አጠባበቅ መርሆዎች በመከተል ሥራዎቹን ያከናውናል፡፡ ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፰ ስለ ሂሣብ ዓመት፣ የሂሣብ አዘጋግና ስለ ዓመታዊ ዘገባዎች**

፩ የየትኛውም ድርጅት የሂሣብ ዘመን በተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የሚወሰን ይሆናል፤

፪ የትኛውም ድርጅት ቢያንስ በሂሣብ ዓመቱ አንድ ጊዜ ሂሣቡን መዝጋት አለበት፡፡ ሂሣቡን የመዝጋቱ ተግባር የሂሣብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በሦስት (፫) ወር ጊዜ ውስጥ መፈፀም ይኖርበታል፤

፫ ድርጅቱ ወደ ፊት የሚኖሩትን እቅዶች፣ክንውኖችና ፕሮግራሞች ጨምሮ ባለፈው የሂሣብ ዓመት ስላከናወናቸው ተግባራትና ስለፈፀማቸው ጉዳዮች ዘገባዎችን ያዘጋጃል፤

፬ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፪/ ስር በተደነገገው መሠረት ዓመታዊ ሂሣብን በወቅቱ አለመዝጋት ወይም ይህንኑ ከማከናወን ችላ ማለት በድርጅቱ ስራ አመራር ላይ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

**፳፱ ስለመጠባበቂያ ሂሣቦችና አጠቃቀማቸው**

፩ የትኛውም ድርጅት ህጋዊ የመጠባበቂያ ሂሣብ ይመሰርታል፣ ይይዛል፤

**PART SIX**
**ACCOUNTING AND CONTROL SYSTEM OF PUBLIC ENTERPRISES**

**SUBSECTION ONE**
**ACCOUNTS OF PUBLIC ENTERPRISES**

**27. Accounting Principles**

Any public enterprise shall carry out its activities and maintain records by following generally accepted accounting principles. The supervisory authority may issue necessary guidelines to implement the same.

**28. Accounting Period, Closing of Accounts, and Financial Reports**

1) The accounting period of any public enterprise shall be determined by the supervisory authority;

2) Every public enterprise shall close its accounts at least once in a financial year. The annual closing of accounts shall be completed within three (3) months following the end of the financial year.

3) The public enterprise shall prepare a report on the state of its activities and affairs during the last financial year, including a statement of achievements and future plans, events, and programs.

4) Failure to close the annual accounts in due time or negligence to do so shall result in liability on the enterprise's management as stipulated under sub-section /2/ of this article.

**29. Reserve Accounts and their Utilization**

1) Any public enterprise shall establish and maintain a legal reserve account;

፪ በሌላ ህግ በተለየ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ድርጅት ከተጣራው ትርፍ ላይ ፭ በመቶ የሚሆነውን ሂሣብ በየዓመቱ እያነሳ የህጋዊ መጠባበቂያው ሂሣብ የድርጅቱን ካፒታል ፳ በመቶ እስኪደርስ ድረስ ወደ መጠባበቂያ ሂሣቡ ያስገባል፤

፫ ህጋዊ የመጠባበቂያ ሂሣቡ የሚከተሉትን ለመሸፈን በጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡-

ሀ/ በድርጅቱ ላይ የደረሱ ኪሣራዎችን፤
ለ/ ያልተጠበቁ ወጭዎችንና ዕዳዎችን፡፡

፬ የማናቸውም ድርጅት ቦርድ በተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የቅድሚያ ስምምነት ሌሎች የመጠባበቂያ ሂሣቦች እንዲያዙ ለማድረግና አጠቃቀማቸውን ለመወሰን ይችላል፡፡

**፴ <u>ስለ ግብር እና ቀረጥ አከፋፈል</u>**

፩ የግብር እና ቀረጥ ክፍያዎችን በሚመለከት አስቀድመው የወጡና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ህጐች በድርጅቶች ላይም ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፤

፪ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /፩/ ስር የሰፈረው ድንጋጌ ድርጅቶች በሌላ ህግ መሠረት ከግብርና ቀረጥ ነፃ ለመሆን ያሏቸውን መብቶችና ጥቅሞች አያስቀርባቸውም፡፡

**፴፩ <u>ስለክልሉ መንግስት የትርፍ ድርሻ ክፍያ</u>**

የዚህ አዋጅ አንቀፅ /፲፫/ ንዑስ አንቀፅ /፰/ እንደተጠበቀ ሆኖ የትኛውም ድርጅት የሂሣብ ዓመቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ሰባት (፯) ወራት ጊዜ ውስጥ የክልሉን መንግስት የትርፍ ድርሻ ፈሰስ ያደርጋል፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>**

**<u>ስለ ሂሣብ ምርመራና ቁጥጥር</u>**

2) Without prejudice to the provisions provided in other laws otherwise, any public enterprise shall annually transfer 5% of its net profit to the legal reserve account until such reserve account reaches 20% of the enterprise's capital;

3) The legal reserve account shall be used to cover the following:

   a) Losses incurred by the enterprise;
   b) Unforeseen expenses and liabilities.

4) The board of any public enterprise shall, with the prior consent of the supervisory authority, establish other reserve accounts and determine their use.

**30. <u>Payment of Taxes and Duties</u>**

1) Laws that have already been issued regarding the payment of taxes and duties and are relevant to the issue shall be applicable to public enterprises;

2) The above provision under sub-article /1/ shall not deprive public enterprises of their rights and benefits to be exempted from taxes and duties under any other law.

**31. <u>Payment of Dividend to the State Government</u>**

Without prejudice to the provision of sub-article /8/ of Article /13/ of this proclamation, any public enterprise shall pay the profit share of the state government within seven (7) months following the end of the financial year.

**<u>SUBSECTION TWO</u>**

**<u>AUDITING AND CONTROL OF ACCOUNTS</u>**

**፴፪ ስለ ኦዲተሮች አሿሿም**

፩ በሌላ ህግ ለክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የማናቸውም ድርጅት ሂሣብ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች ይመረመራል፤

፪ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፩/ መሠረት የሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የወጡ መመዘኛዎችን የሚያሟሉና ከማናቸውም ዓይነት ተፅዕኖ ነፃ የሆኑ መሆን ይኖርባቸዋል፤

፫ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የውጭ ኦዲተሮችን የአገልግሎት ዘመን ይወስናል።

**፴፫ የመተባበር ግዴታ**

የተመርማሪውን ድርጅት ገንዘብ ወይም ንብረት የተረከበ፣ ወጭ ያደረገ፣ የከፈለ ወይም ለሂሣቡ ሀላፊ የሆነ ማንኛውም ሰው ስለ ጉዳዩ በሚጠየቅበት ጊዜ ሂሣቡን የማስመርመርና አስፈላጊውን መረጃ የመስጠት ወይም የማቅረብ ግዴታ አለበት።

**፴፬ ስለኦዲተሮች ስልጣን፣ ተግባርና ተጠያቂነት**

የኢትዮጵያ ንግድ ህግ ቁጥሮች /፫፻፸፫/፣/፫፻፸፬/፣/፫፻፸፭/፣/፫፻፸፮/፣/፫፻፸፰/ እና /፫፻፹/ እንደተገቢነቱ አስፈላጊው ለውጥ ወይም ማስተካከያ እየተደረገባቸው የማናቸውንም ድርጅት ኦዲተሮች ስልጣን፣ ተግባርና ተጠያቂነት በተመለከተ በተመሣሣይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ።

**32. Appointment of Auditors**

1) Subject to the powers and functions given to the Office of the Chief Auditor of the State by other laws, the accounts of any public enterprise shall be examined by the external auditors appointed by the supervisory authority;

2) The external auditors appointed by the supervisory authority in accordance with sub-article /1/ of this article shall meet the standards issued by the regional auditor's office and must be free from any kind of influence;

3) The supervisory authority shall determine the term of service of the external auditors.

**33. Duty to Cooperate**

Any person who has received, paid or expended for or is in charge of the accounts of the money or property of the enterprise being audited, when requested, shall have the obligation to provide the accounts to be audited and to furnish the necessary information to the auditors.

**34. Powers, Duties and Responsibilities Auditors**

Articles /373/, /374/, /375/, /376/, /378/ and /380/ of the Commercial Code of Ethiopia shall be applied in the same way with the necessary changes or adjustments as deemed appropriate with regard to the powers, duties, and responsibilities of auditors of any public enterprise.

## ክፍል ሰባት

## ድርጅቶች ስለሚዋሀዱበት ወይም ስለሚከፋፈሉበት ሁኔታ

**፴፭ መርህ**

## PART SEVEN

## MERGER OR SPLIT-OFF OF PUBLIC ENTERPRISES

**35. Principle**

፩ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ድርጅቶች አንደኛው ሌላውን በማጠቃለልም ሆነ አንድ ሌላ አዲስ ድርጅት በመፍጠር በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ውሣኔ ሊዋሀዱ ይችላሉ፤

፪ አንድ ድርጅት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ አዳዲስ ድርጅቶችን ለመፍጠር በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ውሣኔ ሊከፋፈል ይችላል፤

፫ በዚህ አዋጅ መሠረት የማዋሀዱም ሆነ የመከፋፈሉ ውሣኔ ተግባራዊ የሚደረገው በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ አማካኝነት ይሆናል።

**፴፮ የወል ድንጋጌዎች**

፩ ከባለገንዘቦች ጋር የብድር ስምምነት ያደረገና ዕዳውን ገና ያልከፈለ ማናቸውም ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት ከመዋሀዱ ወይም ወደ ሌሎች አዳዲስ ድርጅቶች ከመከፋፈሉ በፊት የአበዳሪውንና የዋስትና ሰጭውን ስምምነት መጠየቅ ይኖርበታል፤

፪ በዚህ አዋጅ መሠረት እንዲዋሀድ ወይም ወደሌሎች አዳዲስ ድርጅቶች እንዲከፋፈል የታሰበ ማናቸውም ድርጅት አስቀድሞ ዕዳ ያለበት ሆኖ ሲገኝ በውህደቱ ወይም በክፍፍሉ ምክንያት እንደአዲስ የሚፈጠረው ድርጅት በገንዘብ ጠያቂዎች በኩል የሚፈለግበትን ዕዳ ለመክፈል የማይችል ስለ መሆኑ የታወቀ እንደሆነ የመዋሀዱም ሆነ የመከፋፈሉ ውሣኔ ሊሰጥ አይችልም፤

፫ የሚዋሀደው ወይም የሚከፋፈለው ድርጅት ካለፈው ግማሽ ዓመት መጀመሪያ አንስቶ ውህደቱ ወይም ክፍፍሉ እስከተፈፀመበት ጊዜ ድረስ ያለው ሂሣብ በኦዲተር ይመረመራል።

**፴፯ መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ**

፩ በውህደት ምክንያት ህልውናውን ያጣ የመጀመሪያ ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች እርሱን ወደሚያጠቃልለው ወይም በውህደቱ ምክንያት

1) Two or more public enterprises can be merged by the decision of the regional government administrative council either by merging the other or by creating another new public enterprise;
2) An public enterprise may be split into two or more new public enterprises by the decision of the regional government administrative council;
3) According to this decree, the decision of the merger or split-off will be implemented through a regulation issued by the regional government administrative council.

**36. Common Provisions**

1) Any public enterprise that has entered into a loan agreement with investors and has not yet paid the debt must seek the consent of the lender and the guarantor before merging or splitting-off into other new public enterprises in accordance with this decree;
2) According to this decree, when any enterprise that is intended to be merged or split-off into other new public enterprises is already in debt, the decision of the merger or split-off cannot be given because the new enterprise created as a result of the merger or split-off is unable to pay the debts demanded by the creditors;
3) The accounts of the public enterprise to be merged or split-off from the beginning of the previous half year to the time of the merger or split-off shall be examined by the auditor.

**37. Transferring Rights and Obligations**

1) The rights and obligations of the first enterprise that has lost its existence due to the merger shall be transferred to the new enterprise that includes it or is

ወደሚፈጠረው አዲስ ድርጅት ይተላለፋሉ፤

፪ በዚህ አዋጅ መሠረት ከአንድ በላይ ወደሆኑ አዳዲስ ድርጅቶች የተከፋፈለ ማናቸውም ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች ወደሚፈጠሩት አዳዲስ ድርጅቶች ይተላለፋሉ፡፡

**፴፰ በክፍፍል ወቅት ስለሚኖር የመብቶችና ግዴታዎች ድልድል**

፩ በመከፈል ላይ ያለ ማናቸውም ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች ወደ አዳዲሶቹ ድርጅቶች የሚደላደሉት ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በሚወስነው መሠረት ይሆናል፤

፪ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የድርጅቱን መከፈል ውሣኔ የያዘና የቀድሞ መብቶችና ግዴታዎቹ በክፍፍሉ ምክንያት አዲስ በተፈጠሩት ድርጅቶች መካከል እንደተደላደሉ የሚያሳይ የተሟላ ሪፖርት ያዘጋጃል፤

፫ የዚሁ ሪፖርት አንድ ቅጅ በክፍፍሉ የተፈጠረው እያንዳንዱ ድርጅት በሚቋቋምበት ጊዜ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይቀርባል፣ የክፍፍሉ ውጤት የሆነው እያንዳንዱ ድርጅትም የሪፖርቱን አንዳንድ ቅጅ ያገኛል፤

፬ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የሪፖርቱን ዋና ዋና ነጥቦች የያዘ መግለጫ በሰፊው በሚሰራጩ ጋዜጦች አማካኝነት በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል፤

፭ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ /፩/ እስከ /፬/ ድረስ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ቢኖሩም በክፍፍሉ የተፈጠሩት ድርጅቶች ሁሉ የተከፈለው ድርጅት ለሶስተኛ ወገኖች የገባውን ግዴታ በሚመለከት በአንድነትና በነጠላ ሀላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

created as a result of the merger;

2) The rights and obligations of any public enterprise split-off into more than one new public enterprise pursuant to this decree shall be transferred to the new public enterprises created.

**38. Allocation of Rights and Obligations at the time of Split-Off**

1) The rights and obligations of any public enterprise in split-off shall be transferred to the new public enterprises as determined by the supervisory authority;
2) The supervisory authority shall prepare a complete report containing the decision of the split-off of the enterprise and showing that the former rights and obligations have been mediated between the newly created enterprises as a result of the split-off;
3) A copy of the same report shall be submitted to the regional government administrative council at the time of establishment of each public enterprise created by the split-off, and each public enterprise that is the result of the split-off will receive a copy of the report;
4) The supervisory authority shall publish a statement containing the main points of the report in widely circulated newspapers in Amharic and English languages;
5) Notwithstanding the provisions of sub-articles /1/ to /4/ of this article, all the public enterprises created by the split-off shall be jointly and severally responsible for the obligations to third parties of the enterprise before split-off.

## ክፍል ስምንት

## PART EIGHT

## DISSOLUTION AND WINDING-UP OF PUBLIC

## ድርጅቶች ስለሚፈርሱበትና ሂሣባቸው ስለሚጣራበት ሁኔታ

### ፴፱ ድርጅት ስለሚፈርስባቸው ምክንያቶች

ማናቸውም ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ወይም በሌላው ሊፈርስ ይችላል፡-

፩ በማቋቋሚያ ደንቡ የተመለከተው የድርጅቱ መዋዕለ-ዘመን ሲያበቃ፤

፪ ድርጅቱ የተቋቋመበት ዓላማ ወይም ተልዕኮ ሲፈፀም፤

፫ ድርጅቱ የተቋቋመበት ዓላማ ሲከሽፍ ወይም ሊፈፀም የማይችል ሆኖ ሲገኝ፤

፬ ከመቶ ፸፭ እጅ የሚሆነውና አስቀድሞ የተከፈለው የድርጅቱ ካፒታል ሲጠፋ፤

፭ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የድርጅቱን ህልውና የሚነካ ማናቸውንም ዓይነት ውሣኔ ሲያሳልፍ ፤

፮ የድርጅቱ መክሰር በፍርድ ቤት ሲወሰን፡፡

### ፵ በመክሰር ወቅት ስለሚከናወን የሂሣብ ማጣራት ተግባር

፩ የመክሰር ስርዓትን በሚመለከት እንደአስፈላጊነቱ የኢትዮጲያ ንግድ ህግ ፭ኛ መፅሀፍ ድንጋጌዎች አስፈላጊው ለውጥ ወይም ማስተካከያ እየተደረገባቸው በድርጅቶች ላይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፤

፪ በኢትዮጵያ ንግድ ህግ ቁጥር /፲፻፷፮/ ከንዑስ አንቀጽ /፩/ እስከ /፪/ ድረስ የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ የድርጅት መክሰር በንግድ ህግ መሠረት በአጭር ስነ-ስርዓት እንዲመራ ሊወስን ይችላል፡፡

### ፵፩ ስለ ሂሣብ አጣሪዎች አሿሿም፣ ስልጣንና ተግባር

## ENTERPRISES

### 39. Reasons for the Dissolution of Public Enterprises

Any public enterprise may be dissolved for one or other of the following reasons:

1) When the term of the public enterprise specified in the establishment regulation ends;
2) When the public enterprise's purpose or mission is accomplished;
3) When the purpose for which the public enterprise was established fails or cannot be fulfilled;
4) When 75 percent of the capital of the enterprise that has been paid in advance is lost;
5) When the regional government administrative council passes any decision affecting the public enterprise's existence;
6) When the enterprise's bankruptcy is decided by the court.

### 40. Auditing of Accounts During Bankruptcy

1) The provisions of the 5th Book of the Ethiopian Commercial Code regarding the bankruptcy system shall be applicable to the public enterprises subject to the necessary changes or adjustments;
2) Notwithstanding the provision of Article /1166/ sub-articles (1) to (2) of the Commercial Code of Ethiopia, the court may decide that bankruptcy proceedings of a public enterprise be conducted by way of a short procedure.

### 41. Appointment, Powers and Duties of Liquidators

1) In the event of the situations referred to in sub-

፩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ /፴፱/ ከንዑስ አንቀፅ /፩/ እስከ /፭/ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የወጡትን መመዘኛዎች የሚያሟላና የድርጅቱ ሰራተኛ ያልሆነ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሂሳብ አጣሪዎችን ይሾማል፤ በቂ ምክንያት ሲያጋጥም ደግሞ ሂሳብ አጣሪዎቹን ሊሽርና በምትካቸው ሌሎችን ሊሾም ይችላል፤

፪ ሂሳብ አጣሪዎች በመፍረስ ላይ ያለውን ድርጅት መዛግብትና የሂሳብ ሰነዶች ይረከባሉ፤

፫ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በሌላ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ሂሳብ አጣሪዎቹ በዚህ አዋጅ መሠረት የድርጅቱን ንብረት በመረከብ ለቦርዱና ለዋና ስራ አስኪያጁ የተሰጧቸውን ስልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላሉ፡፡ ሆኖም ሂሳብ አጣሪዎቹ ያልተቋጩ ውሎች ከሚጠይቁት አፈፃፀም ወይም ለሂሳብ ማጣራቱ አስፈላጊ ሆነው ከተገኙት በስተቀር አዳዲስ የንግድ ስራዎችን ሊጀምሩ አይችሉም፤

፬ ቦርዱ ካለፈው የሂሳብ ዓመት መጨረሻ ጀምሮ የሂሳብ ማጣራት ተግባሩ እስከተጀመረበት ቀን ያለውን ጊዜ የሚሸፍንና የድርጅቱን ጉዳዮች የሚመለከት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሂሳብ አጣሪዎች እንዲደርሳቸው ያደርጋል፤

፭ ሂሳብ አጣሪዎችና ቦርዱ የድርጅቱን መብቶችና ግዴታዎች ባጭሩ የያዘ መግለጫ በጋራ አዘጋጅተው ይፈራረሙበታል፤

፮ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ቦርዱና የድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ሂሳብ አጣሪዎቹን በስራቸው ያግዟቸዋል፡፡

articles /1/ to /5/ in Article /39/ of this decree, the supervisory authority shall appoint one or more liquidators who meet the standards issued by the regional auditor's office and who are not employees of the organization; when there is a sufficient reason, the supervisory authority may cancel the liquidators and appoint others in their place;

2) The liquidators shall take possession of the records and accounting documents of the enterprise in liquidation;

3) Unless the supervisory authority decides otherwise, the liquidators shall take possession of the enterprise's assets and exercise the powers and duties given to the board and the general manager in accordance with this decree. However, the liquidators may not initiate new business activities except for the execution of contracts still running or as deemed necessary for the liquidation;

4) The board shall prepare a report covering the period from the end of the previous accounting year to the date of the commencement of the liquidation and shall provide the liquidators with a report on the enterprise's affairs;

5) The liquidators and the board jointly prepare and sign a statement that summarizes the enterprise's rights and obligations;

6) Unless otherwise decided by the supervisory authority, the board and the general manager of the enterprise shall assist the liquidators in their work.

**42. <u>Calling On Creditors</u>**

1) The liquidators shall have a responsibility to inform creditors of the proposed dissolution of the

**፴፪ <u>ባለገንዘቦችን ስለመጥራት</u>**

፩ ሂሣብ አጣሪዎች ድርጅቱ የሚፈርስ መሆኑን በመግለፅ ያላቸውን የገንዘብ ጥያቄ በተገቢው የሰነድ ማስረጃ አስደግፈው ያቀርቡ ዘንድ ለባለገንዘቦች የማሳወቅ ሀላፊነት አለባቸው፤

፪ ስማቸው በድርጅቱ መዝገብ ተይዞ ለሚገኘው፣ እንዲሁም በሌላ ሁኔታ ለታወቁ ባለገንዘቦች ተገቢ ሆኖ የተገኘው ማስታወቂያ በሪኮማንዴ ደብዳቤ ይላክላቸዋል፤

፫ ሌሎች ባለገንዘቦች ደግሞ በሰፊው በሚሰራጭ የክልሉ ጋዜጣ በየሣምንቱ በሚወጡ ሶስት ተከታታይ ማስታወቂያዎች ይህንኑ እንዲያውቁት ይደረጋል፤

፬ ባለገንዘቦች ያላቸውን የገንዘብ ጥያቄ እንደነገሩ ሁኔታ ደብዳቤ ከደረሳቸው ወይም የመጨረሻው የጋዜጣ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ ፺ (ዘጠና) ቀናት ውስጥ የገንዘብ ጥያቄዎቻቸውን እንዲያቀርቡ ይደረጋል፤

፭ የሂሣብ አጣሪዎች ስለ ድርጅቱ የሂሣብ እንቅስቃሴ ተገቢውን መግለጫ አዘጋጅተው ስለዕዳው አከፋፈል ያላቸውን ሐሳብ፣ ስለ ባለገንዘቦች ዝርዝርና የአከፋፈላቸው ቅደም ተከተል የሚኖር ከሆነም በመጨረሻ ለተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ያቀርባሉ፤

፮ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ሂሣብ አጣሪዎች ያዘጋጁትን የሂሣብ እንቅስቃሴ መግለጫ መሰረት በማድረግና ለአከፋፈል ያቀረቡትን ሀሣብ በማመዛዘን፦

ሀ/የገንዘብ ጥያቄያቸውን በማስረጃ በማስደገፍ ላቀረቡ ባለገንዘቦች ክፍያው እንዲፈፀም ያዛል፤

ለ/ የድርጅቱ ጥሬ ገንዘብ ለባለገንዘቦች መክፈል

enterprises and require them to file their claims with appropriate supporting documents;

2) Notification shall be sent by registered letter to the creditors whose names are registered in the enterprise's register, as well as to the creditors who are otherwise known;

3) Other creditors shall be notified by notice published in three successive weekly issues of a regional newspaper of the general circulation;

4) Creditors shall be required to submit their claims within 90 (ninety) days from the date of receipt of the letter or from the date of the last issue of the notice in the newspaper, as the case may be;

5) The liquidators shall then prepare and submit to the supervisory authority, the appropriate financial statement of the enterprise together with their recommendations and a list of creditors and priorities, if any, according to which such payments are to be made;

6) The supervisory authority shall, on the basis of the financial statement prepared by the liquidators and after taking into consideration their recommendations:

   a) Order the payment of creditors who have filed their claims with the necessary proof;

   b) Where the cash balances of the enterprises are not sufficient to cover the debts due to the creditors , authorize the liquidators to sell assets of the enterprise by using methods approved by

ያለበትን ዕዳ የማይሸፍን ሆኖ ሲገኝ የሶስተኛ ወገኖችን መብት ሣይነካ እርሱ በሚያፀድቀው የሽያጭ ዘዴ የሂሣብ አጣሪዎች የድርጅቱን ንብረቶች እንዲሸጡ ሊፈቅድ ይችላል፤

፯ ጠቅላላው ንብረት ዕዳውን ለመክፈል የማይችል ሆኖ በሚገኝበት ጊዜና የተፈቀደው ካፒታል በሙሉ ሣይከፈል የቀረ እንደሆነ፣ ሂሣብ አጣሪዎች ቀሪው ካፒታል እንዲከፈል ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑን ይጠይቃሉ።

## ፵፫ የባለ ገንዘቦችን መብት ስለመጠበቅ

፩ የታወቁ ባለገንዘቦች በዚህ አዋጅ አንቀጽ /፵፪/ ንዑስ አንቀጽ /፪/ እና /፫/ ስር በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ የገንዘብ ጥያቄያቸውን ሣያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ሊከፈላቸው የሚገባው ገንዘብ በባለ ገንዘቦቹ ስም በባንክ ተቀማጭ ይደረጋል፤

፪ ባልተጠናቀቁ የድርጅቱ ስራዎች መነሻነት የሚቀርቡ የገንዘብ ጥያቄዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ እንዲሁም ባለገንዘቦቹ ዋስትና ያልተሰጣቸው ከሆነ ክርክር ያስነሱ እዳዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ ክርክሩ እስከሚወሰንበት ቀን ድረስ ለብቻ ተቀማጭ ሆኖ ይያዛል፤

፫ በዚህ አዋጅ አንቀፅ /፵፪/ ንዑስ አንቀፅ /፪/ መሠረት የድርጅቱ ህልውና ካከተመ በኂላ የቀረበና በድርጅቱ መዝገብ ያልታወቀ ማናቸውም ዕዳ ባለገንዘቦች የገንዘብ ጥያቄያቸውን ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ /፪/ ስር በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሣያቀርቡ የቀሩት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የሆነ እንደሆነ በትርፍነት ለክልሉ መንግስት ከገባው ሀብት ላይ ተቀናሽ ሆኖ እንዲከፈላቸው ሊጠይቁ ይችላሉ። እንዲሁም በሂሳብ

him without affecting the rights of third parties;

7) Where the total assets of the enterprise are not sufficient to pay off its debts and the authorized capital is not fully paid up, the liquidators shall ask the supervisory authority for the full payment of the capital.

## 43. Protection of the Rights of Creditors

1) Where known creditors have failed to file their claims within the time limit specified in Article 42 sub-articles /2/ and /3/ of this proclamation, the amounts due to them shall be deposited with a bank to the names of the creditors.

2) Sums shall be set aside to meet claims respect of undertakings of the enterprise which are not completed or disputed claims where the creditors have not been guaranteed until the dispute is settled.

3) Notwithstanding the provisions of Article 42 sub-articles /2/ of this proclamation, after the enterprise ceased to exist, creditors not appearing in the books of the enterprise may claim from the surplus assets collected by the Government, provided their failure to claim within the time-limit was due to force majeure. Creditors may claim against the liquidators, where they have not been paid owing to the liquidators' negligence.

## 44. Final Balance Sheet and Announcing the

አጣሪዎች ቸልተኝነት ምክንያት ዕዳው ያልተከፈላቸው ባለገንዘቦች ሂሣብ አጣሪዎችን በሀላፊነት ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

**፵፬ የመጨረሻ የሀብትና ዕዳ መግለጫና የድርጅቱን መፍረስ ስለማስታወቅ**

፩ ባለገንዘቦች ገንዘቡ ከተከፈላቸው በኂላ ሊቀርቡ የሚችሉ የገንዘብ ጥያቄዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ በዚህ አዋጅ አንቀጽ /፵፫/ ንዑስ አንቀፅ /፪/ መሠረት ተቀማጭ ከሆነ በኂላ ሂሣብ አጣሪዎች ድርጅቱ ትርፍ ሀብት ካለው ይህንኑ የሚያሳይ የመጨረሻ የሀብትና የዕዳ መግለጫ አዘጋጅተው ለተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ያቀርባሉ፡፡ ይህንኑ ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ እንዲሁም ለክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በግልባጭ ያሳውቃሉ፤

፪ የክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት አንዳች አስተያየት ቢኖረው ይህንኑ ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮም ሆነ ለተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ወዲያውኑ ይሰጣል፣

፫ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የክልሉን ፋይናንስ ቢሮ የቅድሚያ ስምምነት ካገኘ በኃላ የመጨረሻውን የሀብትና የዕዳ መግለጫ ሲያፀድቀው ወዲያውኑ ድርጅቱ እንዲፈርስ መፈለጉን ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያሳውቃል፤

፬ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትም ድርጅቱ የተቋቋመበትን ደንብ ይሰርዛል፣ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮም የድርጅቱ ህልውና ያከትማል፤

፭ የፈረሰው ድርጅት መዛግብት በተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ዘንድ ተቀማጭ ሆነው ለአስር (፲) ዓመታት ያህል ይቆያሉ፡፡ እነዚህን መዛግብት ለማየት የሚፈልጉ ሰዎችም ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል ማየትና መመርመር ይችላሉ፡፡

**፵፭ ለመንግስት ገቢ ስለሚሆኑ ሀብቶች**

**Dissolution of the Enterprise**

1) After the creditors have been paid or sums have been set aside to meet potential claims pursuant to Article /43/, sub-article/2/ of this proclamation, the liquidators shall prepare a final balance sheet showing surplus assets, if any, and submit it to the supervisory authority. With a copy, they will notify the same to the Regional Finance Bureau and the Regional Auditor General Office;
2) The Regional Auditor General shall promptly forward his comments, if any, to the Regional Finance Bureau as well as to the supervisory authority;
3) After obtaining the prior consent of the Regional Finance Bureau, the supervisory authority approves the final balance sheet, and shall submit the dissolution proposal to Regional Government Administrative Council for approval.
4) The Regional Government Administrative Council shall then repeal the establishment regulations of the enterprise; the enterprise shall cease to exist as of the date of repeal of its establishment regulations;
5) The books of the dissolved enterprise shall be deposited with the supervisory authority where they shall be kept for ten (10) years. Any interested person may see and inspect such books after payment of the prescribed fee.

**45. Assets Due to the Government**

According to this proclamation, surplus assets of any public enterprise that has been dissolved and whose accounts have been audited, if any, shall be devolved to the state government.

| | |
|---|---|
| በዚህ አዋጅ መሠረት የፈረሰና ሂሣቡ እንዲጣራ የተደረገ ማናቸውም ድርጅት ትርፍ ሀብት ቢኖር ለክልሉ መንግስት ገቢ ይሆናል፡፡ | |
| **ክፍል ዘጠኝ**<br>**ስለ መንግስት ልማት ድርጅቶች ድጋፍና ክትትል ተቆጣጣሪ ባለስልጣን መቋቋምና ስልጣን**<br><br>**፵፮ ስለ መቋቋም**<br><br>፩ የክልሉ መንግስት ልማት ድርጅቶች ድጋፍና ክትትል ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ከዚህ በኃላ **"ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ"** እየተባለ የሚጠራው የክልሉ መንግስት ከፍተኛ አመራር የያዘ ተቋም በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤<br><br>፪ የተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ አይነተኛ ተልዕኮ በክልሉ ውስጥ የሚቋቋሙትን የመንግስት ልማት ድርጅቶች አማክሎ መምራት፣ መደገፍና የክልሉ መንግስት በነዚሁ ተቋማት ላይ ያለውን ባለቤትነት ማረጋገጥ ይሆናል፡፡<br><br>**፵፯ የተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ስልጣንና ተግባር**<br><br>ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-<br><br>፩ ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጋር የቅድሚያ ምክክር በማድረግ የድርጅቱን ሥራ አመራር ቦርድ አባላት ሲፈቀድ ይሰይማል፣ እንደአስፈላጊነቱ ከሀላፊነት ያነሣል፤<br><br>፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ መሰረት ከሚሰይማቸው አባላት መካከል መርጦ የቦርዱን ሠብሣቢ ይመድባል፤ | **PART NINE**<br>**ESTABLISHMENT AND POWERS OF PUBLIC ENTERPRISES' SUPERVISORY AUTHORITY**<br><br>**46. Establishment**<br><br>1) The State Government Public Enterprises Support and Monitoring Supervisory Authority, hereinafter referred to as the "Supervisory Authority", an institution with a higher level leadership of the State Government has been established by this proclamation;<br><br>2) The overarching mission of the supervisory authority shall be to uniformly lead and support the public enterprises established in the region and ensure the ownership of the regional government in these enterprises.<br><br>**47. Powers and Duties of the Supervisory Authority**<br><br>The supervisory authority shall have the following powers and duties pursuant to this proclamation:<br><br>1) Appoints the members of the management board of the public enterprise after prior consultation with the head of the regional state, and removes them as necessary;<br><br>2) Selects and assigns the chairperson of the Board from among the members appointed in accordance with the provisions of sub-article (1) of this article;<br><br>3) Determines the allowance to be paid to the members |

| | |
|---|---|
| ፫. ሰብሳቢውን ጨምሮ ለቦርዱ አባላት ሊከፈል የሚገባውን አበል ይወስናል፤ | of the board including the chairperson; |
| ፬. የውጭ ኦዲተሮችን ይሰይማል፤ | 4) Nominates external auditors; |
| ፭. የድርጅቱ መነሻ ካፒታል በክልሉ መንግስት አማካኝነት እንዲመደብ ያስደርጋል፤ | 5) Makes the initial capital of the enterprise be allocated through the state government; |
| ፮. በዚህ አዋጅ አንቀጽ /፳፩/ እና አንቀፅ /፳፪/ ድንጋጌዎች መሠረት የድርጅቱ ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ይወስናል፤ | 6) Decides to increase or decrease the enterprise's capital according to the provisions of article /21/ and article /22/ of this decree; |
| ፯. የድርጅቱ የተፈቀደ ካፒታል በዚህ አዋጅ አንቀጽ /፳/ ንዑስ አንቀፅ /፪/ ስር በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተከፍሎ ይሆን ዘንድ ለዚሁ የሚያስፈልገው የመጠባበቂያ ሂሣብ እንዲመሰረት ወይም ሌሎች ሂሣቦች በክልሉ መንግስት አማካኝነት እንዲመደቡ ያደርጋል፤ | 7) In order for the enterprise's authorized capital to be paid in full within the time frame referred to in Article /20/ Sub-Article /2/ of this decree, makes the necessary reserve account shall be established or other accounts shall be allocated through the state government; |
| ፰. ከቦርዱ በሚቀርብለት ሀሣብና አግባብ ያላቸውን የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ከድርጅቱ የተጣራ ትርፍ ውስጥ በየአመቱ ለክልሉ መንግስት ፈሰስ ሊደረግ የሚገባውን መጠን ይወስናል፤ | 8) Based on the proposal from the board and the relevant provisions of this decree, it determines the amount that should be invested in the state government every year from the enterprise's net profit; |
| ፱. የድርጅቱን የሂሣብና የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች መርምሮ ያፀድቃል፤ | 9) Examines and approves the enterprise's accounting and external audit reports; |
| ፲. በቦርዱ ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የድርጅቱን የኢንቨስትመንት ዕቅድ መርምሮ ያፀድቃል፤ | 10) Examines and approves the enterprise's investment plan that is prepared and presented to by the board; |
| ፲፩. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቁጥጥሩ ስር ያለ ማናቸውም ድርጅት እንዲፈርስ፣ ከሌላ ድርጅት ጋር እንዲዋሀድ ወይም እንዲከፈል፣ ወይም በሽያጭ ወይም በሌላ በማናቸውም ህጋዊ ሁኔታ ወደ ሶስተኛ ወገን እንዲተላለፍ ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ሀሣብ ያቀርባል፣ ያስወስናል፤ | 11) When deemed necessary, for any public enterprise under its control to be dissolved, merged with another public enterprise or liquidated or transferred to a third party through sale or any other legal circumstance, presents the idea to the regional government administrative council as well as makes they shall decide on; |

| | |
|---|---|
| ፲፪ የክልሉ መንግስት ባለ አክሲዮን በሆነባቸው የግል ኩባንያዎች ውስጥ ብቁ የሥራ አመራር ውክልና ማግኘቱን በየጊዜው ይከታተላል፣ ያረጋግጣል<br><br>፲፫ ድርጅቶችን ለመደገፍ፣ ለማሳደግና በውጤታማነት እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ የሚያስችሉ የፖሊሲ ማዕቀፎችን ያዘጋጃል፣ ሥራዎቻቸውን በብቃት ለመፈፀምና እርስ በርስ ለመደጋገፍ የሚረዷቸውን የአሰራር ሥርዓቶች ይዘረጋል፣ ያስተዋውቃል፤<br><br>፲፬ አዳዲስ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ እያጠና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሀሣብ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤<br><br>፲፭ ከቦርዱ ጋር በመመካከር የድርጅቱን ዓመታዊና የረዥም ጊዜ አጠቃላይ ግቦች ያፀድቃል፣ አፈፃፀማቸውን በቅርብ ይከታተላል፤<br><br>፲፮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ /፲፫/ ስር ለቦርዱ የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የክልሉን መንግስት የባለቤትነት መብት ለመጠበቅ ወይም ለማስከበር የሚያስፈልጉትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል። | 12) Regularly monitors and ensures that the state government has qualified managerial representation in private companies in which it is a shareholder;<br><br>13) Prepares policy frameworks to support, grow and enable public enterprises to operate effectively; develops and promotes operational systems that help them to carry out their work efficiently and support each other;<br><br>14) Study the situations for new public enterprises to be established and present proposals to the regional government administrative council; when it is allowed, shall make it put to work.<br><br>15) In consultation with the board, approves the annual and long-term general goals of the public enterprise, closely monitors their implementation;<br><br>16) Under Article /13/ of this Proclamation, it shall carry out other related activities required to protect or enforce the ownership rights of the State Government while maintaining the powers and duties given to the Board. |
| **<u>ክፍል አስር</u>**<br>**<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**<br><br>**፵፰ <u>በሌሎች ህጐች ስለተቋቋሙ ድርጅቶች</u>**<br>፩ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በነባሩ ደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ባወጣቸው ህግጋትና ደንቦች የተቋቋሙ ማንኛዎቹም ድርጅቶች፡-<br>ሀ/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦች አማካኝነት እንደገና እንዲቋቋሙ፣ ተከፋፍለው አዲስ በሚቋቋሙ ድርጅቶች እንዲተኩ ወይም | **<u>PART TEN</u>**<br>**<u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>**<br><br>**48. <u>Public Enterprises Established by Other Laws</u>**<br>1) Any public enterprise established by the laws and regulations issued by the former Southern Nations, Nationalities, and Peoples Region before the issuance of this Proclamation:<br>a) may be re-established, divided and replaced by newly established organizations or merged with other organizations through regulations issued |

ከሌሎች ድርጅቶች ጋር እንዲዋሀዱ፤ ወይም

ለ/ እንደ አስፈላጊነቱ በመስተዳደር ምክር ቤት ዉሳኔ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተቋቋሙ ተቆጥረው በዚህ ህግ ድንጋጌዎች መሠረት እንዲተዳደሩ ሊደረግ ይችላል፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /፩/ ፊደል ተራ ቁጥር /ሀ/ መሠረት የሚቋቋሙ ድርጅቶች አንድን ድርጅት በመከፋፈል ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ድርጅቶችን በማዋሀድ የሚፈጠሩ ሲሆን የተከፋፈለውን ድርጅት ወይም የተዋሀዱትን ድርጅቶች ሂሣብ መዝጋትና መመርመር እንዲሁም መብቶችና ግዴታዎቻቸውን ማስተላለፍን በሚመለከት የዚህ አዋጅ አንቀጽ /፴፯/ እና አንቀፅ /፴፰/ ድንጋጌዎች ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፡፡

## ፵፱ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ልዩ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ ድርጅቶችን ያቋቁማል፣

፪ በተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ አማካኝነት መነሻው ተረጋግጦ ሲቀርብለት ለሚቋቋሙ ድርጅቶች ተፈላጊውን ካፒታል ይመድባል፤

፫ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አንድ ድርጅት እንዲፈርስ፣ ከሌላ ድርጅት ጋር እንዲዋሀድ ወይም እንዲከፋፈል ይወስናል፤

፬ የሶስተኛ ወገኖች መብት ሣይነካ ማናቸውም ድርጅት በኢትዮጵያ ንግድ ህግ መሠረት የንግድ ማህበር ሆኖ

pursuant to this Proclamation; or

b) may be deemed, as necessary, by the decision of the Administrative Council of the region, to have been established in accordance with this decree and be managed in accordance with the provisions of this law.

2) Public enterprise established in accordance with sub-article /1/ (a) of this Article, as they are formed by splitting-off a public enterprise or merging more than one public enterprise, the provisions of this Proclamation stipulated in Article /37/ and Article /38/ concerning the closing and examination of the accounts of the split-off or the merged public enterprise, as well as the transfer of their rights and obligations shall be enforceable.

## 49. Powers and Duties of the Regional Government Administrative Council

According to this proclamation, the Regional Government Administrative Council shall have the following special powers and duties:-

1) Establish public enterprises;

2) Allocate the necessary capital to public enterprises to be established when the origin is confirmed by and presented to it through the supervisory authority;

3) Where it is necessary, it shall determine a public enterprise to be dissolved, amalgamated with other enterprise, or to be split-off thereof;

4) Without affecting the rights of third parties, may permit for any enterprise to be established as a business organization under the Ethiopian

ይቋቋም ዘንድ ሊፈቅድ ይችላል፤

፭. ማናቸውም ድርጅት እንዲሸጥ ወይም በሌላ አኳኋን ማኔጅመንቱ ተለይቶ ወደ ሶስተኛ ወገን እንዲተላለፍ ሊወስን ይችላል፤

፮. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /፬/ ስር እንደተደነገገው አስቀድሞ በተቋቋመ የንግድ ማህበር ውስጥ በክልሉ መንግስት የተያዘ አክሲዬን እንዲሸጥ ወይም በማናቸውም ህጋዊ መንገድ ለሦስተኛ ወገን እንዲተላለፍ ሊወስን ይችላል።

**፶. <u>ስለ ተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**፶፩. <u>ደንቦችና መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን</u>**

፩. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በሚገባ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፤

፪. ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

**፶፪. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ከፀደቀበት ታህሳስ ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አርባ ምንጭ**

**ታህሳስ ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ/ም**

commercial code;

5) May determine any public enterprise to be sold-off or the management in any other manner to be transferred in isolation to third parties;

6) May determine to sell-off shares held by the regional government in business organizations established in advance as stipulated under sub-article /4/ above or to transfer them to a third party in any legal way.

**50. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>**

Any law, regulation, directives or customary practice that contradicts with this proclamation shall not be applicable on matters provided in this proclamation.

**51. <u>Powers to Issue Regulations and Directives</u>**

1) The Regional Government Administrative Council may issue regulations necessary for the proper implementation of this proclamation;

2) The Supervisory Authority may issue such detailed directives as may be necessary for the full implementation of the provisions of this Proclamation and the regulations to be issued pursuant to this Proclamation.

**52. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come to force effective as of December 15, 2023, the date it was presented to and approved by the State Council.

**Arba Minch**

**This 15th Day of December, 2023**

| | |
|---|---|
| **ጥላሁን ከበደ**<br>**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር** | **Tilahun Kebede**<br>**Chief Executive of the South Ethiopia Regional State** |